ለክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ስለ አገር ወዳድነቱና ስለሠራው ድንቅ ነገር ሁሉ «ይበል» የሚያሰኝ ድርጊት ነውና በጎልዳፉ ብዕር መልካም ስሙን ለማንጸባረቅ የተጻፈ ጽሑፍ፣ ይህ ጽሑፍ በስኳር በሽታ ለሚሰቃዩ ወገኖቻችን ገንዘብ ለማሰባሰብ ክቡር ዶክተር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ በምድረ አሜሪካ ሚኒሶታ በመጣ ጊዜ ስለ መልካም ግብሩ የተነበበለት ነው።

## ይኼ ነው ጥላሁን

ታላቅ የዜማ ሰው የወገን መመኪያ፣
ጥላሁን ገሠሠ ክብር ነህ ለኢትዮጵያ።
በስምህ በዝናህ ሁሉም ያከበረህ፣
ለሕፃን ለአዋቂው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነህ።

«ሀብታም ነኝ ሰው አለኝ» ሁልጊዜ የምትለው፣
የምትወደው ሕዝብህ እውነትም ሀብትህ ነው።
ጊዜ አይለውጠውም በአንተ አይፈርስም ቃሉ፣
ዛሬም ምስክር ነው ኢትዮጵያዊው ሁሉ።

ብዕራችን ቢነሣ ዝናህን ለማውሳት፣
ታሪክ ብንመረምር ስላንተ ለማውራት፣
ጥላሁን ገሠሠ «እንዲህ ነው» ለማለት፣
ቃላት አይገልጸውም የአንተን አንተነት።

ምድርህን የምትወድ ሕዝብና አገርህን፣
ዋነኛው ተዋናይ አንተ ነህ ጥላሁን።
በየዘመናቱ ወገን እርቦት አይተህ፣
ችግሩን ተካፍለህ ለቅሶውን አልቅሰህ፣
ያልሰማነው ሰምተን ያላየን እንድናይ፣
በመድረክ ላይ ሳልከው የወገንን ስቃይ።
ባለቀስከው ለቅሶ በአንተ እምባ ውስጥ አልፈን፣
የወገንን ጩኸት ሰቆቃውን አየን።

ታመህ አልጋ ይዘህ «ደክመኻል» ስትባል፣
የአንተ አንደበት ዛሬም ኢትዮጵያን ይጠራል።
አእምሮህ ድንቅ ሀሳብ ለወገን ያፈልቃል፣
ዛሬም ከአንደበትህ ቁም - ነገር ይቀዳል።
ልዩ ሰው ነህና ለአገርህ ለሕዝብህ፣
እንዴት ዓይነት ቃላት ጥላሁን ይገልጽህ።

ኢትዮጵያ ምድሯ ላይ ሲገጥማት ጦርነት፣
ዝናብ ተከልክሎ ረሃብ ሲከሰት፣
ሰላም አልባ ሲሆን ወገንህ ሲጠቃ፣
ክቡር አንደበትህ የኀዘንን ሲቃ፣
እህ! እያለ ሲያለቅስ ሁላችን ሰምተናል፣
ኢትዮጵያን መድረክ ላይ ስትቀርጻት አይተናል።

ችግርዋ ሲያልፍላት ዘርታ ስትሰበስብ፣
ጎተራዋ ሞልቶ በፍሬ ስትጠግብ፣
ደስ ብሏት ስትታይ ምድርዋ ሐሴት ሲሞላ፣
ልጆችዋ ሲያድጉላት ሲማሩ በተድላ፣
አንተ ነህ ጥላሁን ያኔም የገለጽካት፣
ኢትዮጵያን በመድረክ ስትስቅ ያሳየኻት።

ከደሃ ቤተሰብ በችግር ተወልደህ፣
ችግረኛን መርሳት አልሆንልህ አለህ።
የስኳር በሽታ እንዲያ ላሰቃየው፣
ጠቢብ ዘንድ እንዳይሄድ ገንዘብ ለቸገረው፣
ድህነቱ ከብዶት ራሱን ለጣለው፣
ከሰው በታች አርጎ ኑሮ ላስለቀሰው፣
በየቦታው ዞረህ «እርዱኝ» የምትለው፣
ከወገን ጠይቀህ ወገን ለማዳን ነው።

«ደሃ ነኝ የለኝም አቅመ - ቢስ» ነኝ ላለው፣
የአእምሮ ዶክተር ነህ ከጭንቀቱ አዳንከው።

አእምሮህ ድንቅ ሀሳብ ለወገን ያፈልቃል፣
ዛሬም ከአንደበትህ ቁም - ነገር ይቀዳል።
አንተ ታመህ ሳለህ ለአንተ ማሰብ ትተህ፣
እዚህ ምድር መጣህ ውቅያኖስ አቋርጠህ።

ታላቅ የዜማ ሰው የወገን መመኪያ፣
ጥላሁን ገሠሠ ክብር ነህ ለኢትዮጵያ።
በስምህ በዝናህ ሁሉም ያከበረህ፣
ለሕፃን ለአዋቂው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነህ።

ወገን እንዲህ ኩራ እጅግ ተደስተህ፣
ጥላሁን የሚባል አሳቢ ሰው አለህ።
ለችግር የሚደርስ ፈጣን መልእክተኛ፣
ደሃ ሲራብ አይቶ እንቅልፍ የማይተኛ፣
ዘመን ያልቀየረው አስተዋይ ትልቅ ሰው፣
እሱም የወገን ሀብት ወገንም ሀብቱ ነው።
ሕዝቡን እያሰበ የሚኖር እስካሁን፣
የኢትዮጵያ ኩራት ይኼ ነው ጥላሁን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
አብርሃም ሰሎሞን
ታህሣሥ ፴/፲፱፻፺፱